# የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት

# የጋዜጠኝነት የሥነ-ምግባር ደንብ

# (የበይነ መረብ ጋዜጠኝነትን ያካተተ)

**አዘጋጅ ፡- አሻጋሪ ኮንሰልታንሲ**

**ህዳር 2015**

---

**Ashagari Consultancy/ Mekdes Gebrewold Hundura Consultancy**

**Bole sub City, Woreda 02, Ghana Street, P.O. Box , Addis Ababa, Ethiopia Mobile +251937882858 E-mail :-**

# የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት

# የጋዜጠኝነት የሥነ-ምግባር ደንብ

## ማውጫ


መግቢያ

ምዕራፍ አንድ

1/ ትክክለኛነት እና ፍትሐዊነት ........ 1

2/ ነፃነት ........ 2

3/ ሙያዊ ታማኝነት ........ 3

4/ ተጠያቂነት ........ 4

5/ ምላሽ የመስጠት እድል እና እርማት ........ 5

6/ ሚስጥራዊ ምንጮች ........ 6

7/ ሚስጥር መጠበቅ ........ 7

8/ የተሳሳተ ውክልና ይዞ መረጃ መፈለግ ........ 8

9/ ጸያፍ ምስሎችና ጽሑፎች አቀራረብ ........ 9

10/ ለዜና፤ ለፕሮግራምና መጣጥፎች ክፍያ መቀበል ........ 10

11/ የብሔር፣ የሀይማኖት እና የዘር ግጭቶችን መሸፈን ........ 11

12/ ቃለመጠይቆችን እና የስልክ ውይይቶችን መቅዳት........ 12

13/ ሀዘን ነክ ወይም ድንጋጤ የሚፈጥር ዘገባ ........ 13

14/ ሥርዓተ-ፆታ አጠቃቀም ........ 14

15/የፋይናንስ ጋዜጠኝነት ........ 14

16/ ራስን የማጥፋት ሪፖርት ........ 15

17/ ሕፃናት እና አካል ጉዳተኞች ጥበቃ ........ 16

18/ አደንዛዥ እፅና ሱስ ነክ ዘገባ ........ 17

19/ስዕሎችን እና ስሞችን መጠቀም ........ 18

20/ሰብአዊ ክብርን መጠበቅ ........ 19

21/ የዓመፅ ድርጊቶች ........ 20

## መግቢያ

ኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት በሀገሪቱ ውስጥ በመገናኛ ብዙሃን የእርስ በእርስ የቁጥጥር ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግና የጋዜጠኞች የስነ ምግባር ደንብን በማስጠበቅ በኩል በኢትዮጵያ ሚዲያ ፖሊሲና እና በመገናኛ ብዙሃን ዐዋጅ ቁጥር 1238/13 እውቅና ያለው ተቋም ነው፤

የኢትዮጵያ ሚዲያ ካውንስል አንዱ ዋና ተግባር በጋዜጠኞች ዘንድ ከፍተኛ የሙያ ደረጃን ማስተዋወቅ ነው። ምክር ቤቱ ይህንን ተግባሩን ለመወጣት የመገናኛ ብዙሃንን ነፃነትና የሀላፊነት ደረጃን ከማስተዋወቅ እና ከመጠበቅ በተጨማሪ በጋዜጠኞች እና በመገናኛ ብዙሃን የስነምግባር ደንቦችን በማውጣት እንዲተገበሩ አበክሮ ይሰራል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 29 የፕሬስንና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በማረጋገጡ፤

የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 መሠረት ከፍተኛ የሥነ ምግባር ደረጃና ሙያዊ ብቃት ያለው ነፃ፣ ገለልተኛና ብዛሃነት ያለው መገናኛ ብዙሃን የዲሞክራሲያዊ ሂደቱን ለማጠናከር ያላቸውን ሚና በመገንዘቡ፤

የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶችና የጋዜጠኞች ማህበራት የየራሳቸው የሥነ ምግባር ደንቦች ሊኖራቸው ቢችልም በብሔራዊ ደረጃ የሚያገለግል የተቀናጀ አንድ ወጥ የስነ ምግባር ደንብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ፈራሚ የሆኑትን መገናኛ ብዙሃን፤ የበይነ መረብ/ ዲጂታል ሚዲያ ተቋማትና የጋዜጠኞች ሙያ ማህበራት ተግባራትን ለመምራት ይህ ደንብ ወጥቷል፡፡

ትርጓሜ

በዚህ የስነምግባር ደንብ መሠረት "ለዚህ የስነ ምግባር ደንብ ተገዢ የሆነ ሰው" ማለት ጋዜጠኛ፣ የሚዲያ ባለሙያ፣ የውጭ ጋዜጠኛ ወይም የሚዲያ ድርጅት ማለት ነው።

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተጠቀሱት በሙሉ የሴት ፆታንም ያካትታሉ፡፡

**1/ ትክክለኛነት እና ፍትሐዊነት**

1.1/ የዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ጋዜጠኛ ፍትሐዊ ዘገባ ማቅረብ አለበት። ዘገባ በሕዝብ ፍላጎት ጉዳዮች ላይ ሲዘግብ ትክክለኛ እና የማያዳላ መረጃ ማቅረብ አለበት።

1.2/ ጋዜጠኛው መረጃውን ለህዝብ ሲያቀርብ ሁሉም የታሪኩ ገጽታዎችን በተቻለ መጠን በሪፖርቱ ውስጥ ማካተት አለበት፡፡

1.3/ አስተያየቶች ተገቢ ባልሆነ አውድ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች መለየት አለባቸው፤ አስተያየቶቹን ለመለየት የተደረጉ ሙከራዎች በግልፅ ለተደራሲው ሊቀርብ ይገባል።

1.4/ የዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ጋዜጠኛ ወይም የሚዲያ ተቋም ከእውነታው የራቀ ትክክለኛነት እና ፍትሃዊነት የጎደለውን ታሪክ ማተም ወይም ማሰራጨት የለበትም።

1.5/ ለዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ሰው ከወገንተኝነት ነፃ መሆን አለበት፣ በሪፖርቱ ውስጥ በአስተያየት፣ በግምታዊ ዘገባና እና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ ለይቶ ማቅረብ አለበት።

1.6/ ርዕሶች በተቻለ መጠን የታተመውን ወይም የሚሰራጨውን ይዘት ማንፀባረቅ አለባቸው፤ ጋዜጠኞች የተጋነኑና ከይዘቱ ጋር የማይሄዱ ርዕሶችን ከመጠቀም ይታቀባሉ፡፡

1.7/ በመግለጫዎች ውስጥ የተጠቀሱ ውንጀላዎችን ያካተቱ ርዕሶች ተወንጃዩን ወይም ምንጩን መለየት ወይም ቢያንስ በጥቅስ ምልክቶች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡

1.8/ በመግለጫ ውስጥ በአደባባይ የተወነጀሉ ወይም የተተቹ ወይም በአሉታዊ አውድ የተጠቀሱ ሰዎች፣ ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች ምላሽ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ስሙ የተጠቀሰ ሰው ወይም ተወንጃይ ምላሽ መስጠት ካልፈለገም ሙብቱ እንደሚጠበቅለት በመገንዘብ ለህዝብ ማሳወቅ፤ ምላሹ በወቅቱ ካልተገኘ እንደተገኘ እንደሚቀርብ ለተደራሲው ማሳወቅ ይገባል፡፡

1.9/ ለዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ጋዜጠኛ በአደጋ ቦታዎች ተገኝቶ ሲዘግብ ሁሉንም የዜና ተጠቃሾች በአክብሮት መያዝ አለበት፤ በተለይም በወንጀል ወይም በአደጋ ለተጎዱ ሰዎች ርህራሄን ማሳየት አለበት፡፡

1.10/ የዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ጋዜጠኛ የማህበረሰቡን ብዝሃነት በመረዳት ያለ አድልዎ እና ያለ ጭፍን ጥላቻ መረጃውን ለህዝቡ ማሳወቅ አለበት፤ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ መግለጫዎችን፣ አስተያየቶችን እና ተቃራኒ ሃሳቦችን ዐውዱን በጠበቀ መልኩ ሊስተናገዱ ይገባል፡፡

1.11/ የዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ጋዜጠኛ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ሙያዊ ትንታኔ ወይም ዘገባ ማቅረብ ይችላል፤ ትንታኔው የግል ሃሳብን ማካተት የለበትም፡፡

**2/ ነፃነት**

2.1/ ጋዜጠኞች ነፃነታቸውን በመጠበቅ በዜና ይዘት ላይ ተጽእኖ ወይም ቁጥጥር ለማድረግ ከሚሹት ማናቸውም አካላት መከላከል አለባቸው።

2.2/ ለዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ጋዜጠኛ፡-

(ሀ) ዜናዎችን ያለ ፍርሃትና ያለ ስጋት ማሰባሰብ እና ሪፖርት ማድረግ እንዲሁም ከማንኛውም የውጭ ሃይሎች ያልተገባ ተጽእኖን መቃወም፤ አለባቸው፤ ተጽእኖው ከማስታወቂያ አስነጋሪዎች፤ ከምንጮች፤ ከባለ ታሪኮች፤ ከግለሰቦች እና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ቡድኖችን ይጨምራል፡፡

(ለ) የዜና ይዘትን በገንዘብ ለመግዛት ከሚፈልጉ ወይም ፖለቲካዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን ወይም ዜናዎችን ባልተገባ መንገድ ከሚሰበስቡ፤ ከሚያሰራጩ እና ለማስፈራራት የሚሹትን መቋቋምን ይጨምራል፤

(ሐ) የዜና ይዘትን በኤዲቶሪያል ውሳኔ ብቻ መወሰን እና የውጭ ተጽእኖ መቋቋም፡፡

(መ) የጋዜጠኝነት ግዴታን እና የህዝብ አገልግሎትን የሚያዳክም ማንኛውንም የግል ጥቅም ወይም የአቻ ግፊት መቋቋም፤

(ሠ) ዜናን ስፖንሰር የሚያደርግ ድርጅት ይዘትን ለመወሰን፣ለመገደብ ወይም ለመቆጣጠር በምንም መንገድ ዕድል እንዳይኖረው ግንዛቤ መውሰድ፡፡

(ረ) የሚዲያ ተቋሙ ባለቤት ወይም የአስተዳደር አካላት ፍላጎቶች በዜና ዘገባ እና ይዘት ላይ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ መፍቀድ አይገባም።

(ሸ) የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች አንድን አካል በርዕሠ አንቀፃቸው የመደገፍ ወይም የመቃወም ነፃነት ያላቸው ቢሆንም በዜና፤በአስተያየት፣ በፕሮግራምና በማስታወቂያ ስራቸው ገለልተኛ መሆናቸው በግልፅ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡

ቀ/ ጋዜጠኞች በሙያው ውስጥ በሚያደርጓቸው ማንኛውም ተግባራት ውስጥ የመገናኛ ብዙሃንን ነፃነት መጠበቅ አለባቸው፡፡

በ/ ጋዜጠኞች የሙያውን ክብር መጠበቅ አለባቸው፡፡

**3/ ሙያዊ ታማኝነት**

3.1/ ጋዜጠኞች አስቀድመው የታሰቡ የጥቅም ግጭቶችን በማስወገድ በታማኝነት እና በግልፅነት ዜናዎችን ማቅረብ አለባቸው፤ የተመልካቾችን ክብርና እውቀት እንዲሁም የዜና ርዕሰ ጉዳዮችን ያከብራሉ።

በዚህ ደንብ የሚገዛ ሰው፡-

(ሀ) በተቻለ መጠን ምንጮችን ይለያል። ሚስጥራዊ ምንጮች ጥቅም ላይ የሚውሉት ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወይም ለማስተላለፍ በግልጽ ለህዝብ ጥቅም ሲሆን ወይም መረጃ የሚሰጥ ሰው ሊጎዳ በሚችልበት ጊዜ እንደሆነ ይገነዘባሉ።

(ለ) የግል ሃሳብ እና አስተያየቶችን በግልፅ መለየት፤

(ሐ) የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በእውቀት እና በጥንቃቄ መጠቀም ፣ እውነታውን የሚያዛቡ ወይም የክስተቶችን ስሜት የሚቀሰቅሱ ቴክኒኮችን ማስወገድ፤

(መ) የተደበቁ ካሜራዎችን ወይም ማይክሮፎኖችን ጨምሮ ስውር የዜና ማሰባሰቢያ ቴክኒኮችን መጠቀም አይገባም፣ ነገር ግን ለሕዝብ ጠቃሚ የሆኑ ታሪኮችን ለማግኘት ሌላ መንገድ ከሌለ መረጃው የተሰበሰበበትን ቴክኒክ ለተመልካቾች ከተገለፀ በኋላ መጠቀም ይቻላል።

3.2/ ለዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ሰው፡-

(ሀ) በአንድ ዘገባ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ከሆኑ የዜና ምንጮች ገንዘብ በመክፈል መረጃ መውሰድ ፤

(ለ) በዜና ሽፋን ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ከሚፈልጉ ሰዎች ስጦታዎችን፣ ውለታዎችን ወይም ማካካሻዎችን መጠየቅ ወይም መቀበል፤

(ሐ) አቋማቸውን ወይም ነፃነታቸውን ሊጎዱ በሚችሉ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ አይገባም።

(መ) ሆኖም በህግ አግባብ በክፍያ የሚገኙ የመንግስት ሰነዶችን ለመጠቀም ይቻላል፡፡

(ሠ)የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች እንደ ፎቶዎች ወይም ቪዲዮዎች ያሉ ግብአቶችን ለሚያቀርቡ የማካካሻ ክፍያ ሊፈፅሙ እና ሙያዊ ትንታኔና አስተያየት የሚያቀርቡ ባለሙያዎችን በመቅጠር ከሥራቸው ጋር በቀጥታ ለተያያዙ ትንታኔዎች ክፍያ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

**4/ ተጠያቂነት**

የዚህ ህግ ተገዢ የሆነ ሰው ለድርጊቱ ለህዝብ፣ ለሙያው እና ለህሊናው ተጠያቂ መሆኑን ይገነዘባል፤ ስለዚህ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፡-

(ሀ) ሁሉም ጋዜጠኞች እና የሚዲያ ባለሙያዎች እነዚህን ደንቦች እንዲከተሉ በንቃት ማበረታታት፤

(ለ) ለሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፣ ቅሬታዎችን መመርመር እና ስህተቶችን ወዲያውኑ ማረም፤

(ሐ) በሥነ ምግባር መምራት ግዴታ እንዳለባቸው ይገነዘባል።

**5/ ምላሽ የመስጠት እድል እና እርማት**

ለዚህ ደንብ ተገዢ የሆነ ሰው ፡-

5.1/ለተሳሳቱ ነገሮች ተገቢ መልስ ለመስጠት ፍትሃዊና ምክንያታዊ ዕድል  መሰጠት አለበት።

5.2/ ትክክለኛ ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም የተዛባ ታሪክ ታትሞ ወይም ሙተላለፉ ሲታወቅ ወዲያውኑ መታረም አለበት። እርማቶች ትክክለኛውን መረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ስህተቱን ለግልጽነት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር እንደገና ማቅረብ አስፈላጊ አይደለም።

5.3/ በዚህ አንቀጽ ስር የሚደረገው እርማት ከክፍያ ነፃ ነው፤ ለሚታረመው መረጃ ከተሰጠው የአየር ሰዓት ወይም የገፅ መጠን ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረው ይገባል።

5.4/ ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አዘጋጁ የቀረበው ማስተካከያ ወይም ማብራሪያ እውነተኛነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው በማስተባበያው መጨረሻ ላይ ስለማስተባበያው ሀቀኛነት ያለውን ጥርጣሬ የማስፈር መብት /ነፃነት/ አለው፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለው ግን ጥርጣሬውን የሚያፈርስ የፅሁፍ ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በእጁ እስካለ ብቻ ነው፡፡

5.5/የአንድን ዘገባ ስህተት ለማስተካከል ወይም ለማረም የሚቀርበው ጥያቄ በደብዳቤ መልክ ከሆነ፣ አዘጋጁ ሙሉ በሙሉ ወይም ባጠረ መልኩ በተዘጋጀው ቀጣይ እትም ወይም የአየር ጊዜ ሊያወጣው ይችላል፤ በጣም ረጅም እርማት በሆነ ጊዜ  አጭር ማስታወሻ በማዘጋጀት አሳጥሮ የማተም ወይም የማሰራጨት መብት አለው፣

5.6/ የመልሱ አጭር ቅጂ የዋናውን ይዘት ማጣት የለበትም፤

5.7/ በእርስ በእርስ የቁጥጥር ስርዓት ውስጥ የሚዳኝ መገናኛ ብዙሃን የእርማቱ ውሳኔ ወይም ይቅርታ የሚታተመው ወይም የሚሰራጨው በተቻለ መጠን የግልግል ዳኝነት አካሉ ለይቶ ባቀረበው ምክረ ሀሳብ መሆን ይኖርበታል፡፡

**6/ ሚስጥራዊ ምንጮች**

6.1/ ስማቸው ያልተጠቀሱ ምንጮች ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም። ነገር ግን እውነቱን ለማግኘት ሌላ መንገድ እንደሌለ በአርታዒውና በዘጋቢው ሲታመን የሚስጥራዊ ምንጮችን መጠቀም ይቻላል፤

6.2/ በዘጋቢው የሚጠቀሱ የሰነድ ሚስጥራዊ ምንጮች በተዘጋጀው ዘገባ ላይ ጥቅም ላይ ሲውል እነዚህ ምንጮች በታሪኩ ውስጥ መጠቆም አለባቸው።

**7/ ሚስጥር መጠበቅ**

7.1/ መገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች ምስጢራዊ የመረጃ ምንጮችን የመጠበቅ ሞራላዊ ግዴታ አለባቸው፡፡

7.2/ የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞችና አርታኢያን በስራ አጋጣሚ ያገኟቸውን በተለይም ከቢዝነስ፣ ከግለሰብና ከተቋም ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለሶስተኛ ወገን ወይም ተቋም አሳልፈው መስጠት የለባቸውም፡፡

**8/ የተሳሳተ ውክልና ይዞ መረጃ መፈለግ**

ጋዜጠኞች ስራቸውን ሲያከናውኑ እራሳቸውን ይገልፃሉ፤ መረጃን ወይም ምስሎችን በማሳሳት ወይም በማጭበርበር ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር የለባቸውም። ራስን ቀይሮ መረጃ መሰብሰብ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መረጃው በሌላ መንገድ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜና በአርታኢው ሲታመንበት ብቻ ነው።

**9/ ጸያፍ ምስሎችና ጽሑፎች አቀራረብ**

9.1/ በአጠቃላይ የዚህ ሕግ ተገዢ የሆኑ ሰዎች ለዜና ዘገባው የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ጸያፍ ምስሎችንና ጽሑፎችን ማተም አይችሉም።

9.2/ ህብረተሰቡ በዘገባው ውስጥ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው አካላትን፣ ደም አፋሳሽ ድርጊቶች እና አስጸያፊ ትዕይንቶችን መመልከቱ የግድ ካልሆነ በቀር እነዚህን ትዕይንቶች የሚያሳዩ ፎቶግራፎች መታተም ወይም መሰራጨት የለባቸውም።

9.3/ ይህ በሚሆንበት ወቅት የሚሰራጨው መረጃ በጥንቃቄ ሊታይ እንደሚገባ ለተመልካቾችን ወይም ለአንባቢዎች ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይገባል።

**10/ ለዜና፤ ለፕሮግራምና መጣጥፎች ክፍያ መቀበል**

10.1/ በዚህ ህግ የሚገዛ ሰው ማንኛውንም ሰው ግልፅ የሆነ የማስታወቂያ ውል ከሌለ በቀር መረጃ ለማተም ወይም ለማሰራጨት እንደ ማበረታቻ ምንም አይነት ገንዘብ አይቀበልም፡፡

10.2/ ነገር ግን የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት በክፍያ የሚሰሯቸው ፕሮግራሞች ወይም ዓምዶች ካለ ይህንኑ በግልፅ ለተደራሲው በማሳወቅ ማሰራጨት ይችላሉ፡፡

**11/ የብሔር፣ የሀይማኖት እና የዘር ግጭቶችን መሸፈን**

11.1/ የብሔር፣ የሃይማኖት ወይም የዘር ውዝግቦች ዜና፣ አስተያየቶች ወይም የግል ምልከታዎች መታተም ወይም መሰራጨት ያለባቸው እውነታዎች በትክክል ከተረጋገጡ በኋላ እና ተገቢውን ጥንቃቄ ከተደረገ በኋላ ነው፤ የጥንቃቄ እርምጃው ለሀገራዊ መግባባት፣ ለሰላምና ለህዝቦች ወዳጅነት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በሚያመች መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

11.2/ የዜና ዘገባዎች ወይም ሐተታዎች ስሜትን በሚያቀጣጥል፣ ውጥረቱን የሚያባብስ ወይም በሚመለከታቸው ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የሻከረ ግንኙነት በሚያጎላ መልኩ መፃፍም ሆነ መሰራጨት የለባቸውም።

11.3/ ግጭትን የሚያባብሱ ጽሑፎች ወይም ስርጭቶች መወገድ አለባቸው።

**12/ ቃለመጠይቆችን እና የስልክ ውይይቶችን መቅዳት**

12.1/ ተገቢ በሆኑ ጉዳዮች ካልሆነ በቀር ለዚህ ሕግ ተገዢ የሆነ ሰው ግለሰቡ ሳያውቀው ፎቶና ቪዲዮ ማንሳት ወይም ድምፅ መቅዳት አይችልም። ቀረፃው ሊከናወን የሚችለው ጋዜጠኛው በህጋዊ መንገድ ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት መረጃውን ለመሰብሰብ ሳይችል ሲቀርና በአርታዒው ሲታመንበት ብቻ ነው።

12.2/ በስልክ በቀጥታ የሚተላለፉ ውይይቶች ወይም ተቀርፀው የሚቀርቡ መረጃዎች የስልክ ውይይቱ ከመቅረጹ ወይም በቀጥታ ከማሰራጨቱ በፊት፣ ለስልክ ደዋዩ ወይም ተወያዩ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት።

**13/ ሀዘን ነክ ወይም ድንጋጤ የሚፈጥር ዘገባ**

13.1/ የኀዘን ወይም ድንጋጤን በሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ ዘገባ ሲሰራ ጥያቄዎች ከስሜታዊነት በፀዳ እና በማስተዋል መደረግ አለባቸው።

13.2/ በሆስፒታሎች ወይም መሰል ህዝባዊ ተቋማት ውስጥ ጋዜጠኞች ለዘገባ ሲገቡ ጥያቄያቸውን ለሚመለከተው ባለሙያ ከማቅረብ ጀምሮ ማንነታቸውን በመግለጽ ኃላፊነት ካለው የሥራ አስፈፃሚ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

## 14/ ሥርዓተ-ፆታ አጠቃቀም

ሴቶች እና ወንዶች እንደ ዜና ምንጭ በዜናና በሌሎች ፕሮግራሞች እኩል መታየት አለባቸው፤ ይህ ሚዛናዊነት በቁጥር ብቻ የሚገለፅ ሳይሆን ሙያዊ ውክልናን የሚያካትት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፤

## 15/የፋይናንስ ጋዜጠኝነት

15.1/ ጋዜጠኞች ቀድመው የሚያገኟቸውን የፋይናንስ መረጃዎች ለራሳቸው ጥቅም አይጠቀሙበትም፣ መረጃውንም ለሌሎች ማስተላለፍ የለባቸውም።

15.2/ ጋዜጠኞች ፍላጎታቸውን ለአርታዒው ሳይገልጹ እነርሱ ወይም የቅርብ ቤተሰባቸው ከፍተኛ የገንዘብ መዋጮ በሚያደረግባቸው አክሲዮኖች፣ የዋስትና ሰነዶች እና ሌሎች የመገበያያ ሰነዶች ጉዳይ መፃፍ ወይም ማስተላለፍ የለባቸውም።

15.3/ ጋዜጠኞች በቀጥታም ሆነ በውክልና ወይም በቅርብ የቤተሰብ አባላት የተቋቋሙ፣ አክሲዮኖች ወይም ዋስትናዎች ላይ የገበያ ዕቃዎች መግዛት ወይም መሸጥ የለባቸውም። በተለይም በቅርቡ ዘገባ ሊያዘጋጁባቸው ያቀዱት የንግድ ድርጅት ከሆነ አስቀድሞ ለአርታኢው ማሳወቅ ይገባል፡፡

## 16/ ራስን የማጥፋት ሪፖርት

16.1/ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ራስን የማጥፋትን ወንጀልና የአእምሮ ህመምን በጥንቃቄና በኃላፊነት ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

16.2/ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ራስን የማጥፋት ጉዳይን በጥንቃቄና በመቆጠብ ስሜት ማስተናገድ የሚኖርባቸው ሲሆን በዚህም፡-

(ሀ) የሟቹ ቤተሰቦችና ጓደኞች ሕመምን ማባባስ፤

(ለ) ራስን የማጥፋትን ወንጀል ወይም ራስ ላይ ጉዳት ማድረግን አስመስሎ ለመፈጸም የሚያበረታታ ማንኛውንም አይነት ሪፖርት፤

(ሐ) ራስን የማጥፋትን ወንጀል ዝርዝር የአፈጻጸም መንገድ ወይም ቦታን የተመለከተ አላስፈላጊ ማጣቀሻ፤

(መ) ራስን የማጥፋትን ወንጀል በተለይ ወጣት ታዳሚዎች ላይ ያነጣጠረ መገናኛ ብዙሃን ላይ አሳንሶ፣ የተሻለ ወይም የተከበረ አድርጎ የሚያቀርብ ቋንቋን ወይም አቀራረብን፤

(ሠ) የአእምሮ ህመምን ልዩ ልዩ ቅርፆችን የሚገልጹ የተለዩ አነጋገሮችንና እሱን ተከትሎ ሊመጣ የሚችል ለጥቃት የተጋለጡ ሰዎችን ለመገለል አደጋ ሊዳርጉ የሚችሉ መለያዎች መጠቀም፤ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡

(3) የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ራስን የማጥፋትን ወንጀልና የአእምሮ ህመምን ሲዘግቡ ተቀባይነት ያላቸው ማኅበሮችን፣ የምርምር ማዕከሎችን፣ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትንና የጤና ባለሙያዎችን ማማከርና በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡

## 17/ ሕፃናት እና አካል ጉዳተኞች ጥበቃ

17.1/ መገናኛ ብዙሃን የህፃናትንና የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበርና ማበረታታት አለባቸው፡፡

17.2/ ልጆች የወሲብዊ ወንጀሎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች፣ ተጠቂዎች፣ ምስክሮች ወይም ተከሳሾች ሆነው ሊታወቁ አይገባም።
ከሕዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ ካልሆነ በስተቀር በልጆች ላይ የሚደርስ ጥቃት ወይም ወሲብዊ ጉዳይ ያለ ወላጅ ወይም ሌላ አዋቂ ሰው በሌሉበት ጋዜጠኞች ከግል ደኅንነታቸው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ቃለ መጠይቅ ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት የለባቸውም።
17.3/ የአሳዳጊው ወይም ለሕፃኑ ኃላፊነት ያለበት ኀልማሳ ፈቃዱን እስካልሰጠ ድረስ ከ18 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናትን ስለራሳቸው ወይም ስለ ሌላ ሕፃን ደህንነት በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ቃለ መጠይቅ ሊደረግላቸው ወይም ፎቶግራፍ ሊነሱ አይገባም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠያቂው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ከሆነ የህፃናቱ ደህንነት በተጠበቀ መልኩ ሊከናወን ይችላል፡፡

17.4/ የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች እስካልፈቀዱ ድረስ ተማሪዎችን መቅረብ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ፎቶግራፍ ማንሳት አይገባም፡፡ በተማሪዎች ጉዳይ ላይ ትምህርት ቤቱ ወይም የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች ተጠያቂ ከሆኑ የህፃናቱን ደህንነትና መብት በጠበቀ መልኩ ሊከናወን ይችላል፡፡

17.5/ በግልፅ ለህፃኑ ጥቅም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ህፃናትን ደህንነታቸውን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ክፍያ ሊደረግላቸው አይገባም፤ ይህንኑ መረጃ ለማግኘትም ለወላጆቻቸው፣ ለአሳዳጊዎቻቸው ወይም ለጠባቂዎቻቸው ክፍያ ማድረግ አይቻልም፡፡

17.6/ የህፃኑን የግል የህይወት ዝርዝሮች ለማተም አዘጋጆች የወላጆችን ወይም የአሳዳጊን ዝና፤ ክፋት ወይም ደረጃ በምክንያትነት ሊጠቀሙ አይገባም፡፡

17.7/ በሕግ የተፈቀደ ቢሆንም እንኳን መገናኛ ብዙሃን ከ18 ዓመት በታች የሆነ የወሲብ ተጠቂን ወይም የወሲብ ጥቃት ምስክርን ማውጣት /ማተም/ አይገባም፡፡

17.8/ ወንጀል በሚዘገብበት ወቅት ወንጀሉን የተመለከቱ ወይም የወንጀል ተጠቂዎች ሕፃናትን ለአደጋ ያላቸውን ተጋላጭነት አስመልክቶ መገናኛ ብዙሃን ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡

17.9/ ለሕፃናት ተገቢነት የሌላቸው የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ኘሮግራሞች ሲኖሩ ዝግጅቶቹ ሕፃናት ሊያዩዋቸው በማይገቡ ሰዓቶች መተላለፍ የሚገባቸው ሲሆን አስፈላጊ በሆነበት ሁሉ ከእድሜ ጋር የተያያዘ መግለጫ መኖር አለበት፡፡

## 18/ አደንዛዥ እፅና ሱስ ነክ ዘገባ

የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች አደንዛዥ እፅ ጋር የተያያዙ ዘገባዎችን ሲሰሩ የሚከተሉት ጠቅለል ያሉ መመሪያዎች ማገናዘብ ይኖርባቸዋል፡-

(ሀ) በአደንዛዥ እፅ አጠቃቀምና ሱስ ላይ የሚደረጉ ሕዝባዊ ክርክሮችን በኃላፊነት መዘገብ፤

(ለ) ማንኛውም አይነት አደንዛዥ እፅ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች መጋነን ወይም መናናቅ አይኖርበትም፤

(ሐ) ምንም እንኳን ብዙ ወጣቶች በጠቅላላው እውቀቱ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ዝርዝር የአጠቃቀም መንገዶችን ከመግለፅ መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

(መ) በአንዳንድ ሪፖርቶች የአንድ አደንዛዥ እፅን የንጥረ ነገሮች ውህድን መዘርዘር ተቀባይነት ሊኖረው ቢችልም ለማምረት ሊያግዝ የሚችልን ማንኛውንም አይነት ዝርዝር ከማቅረብ መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

(ሠ) ለሞት ሊዳርግ የሚችል የማንኛውንም አይነት አደንዛዥ እፅን መጠን መጥቀስ እና የሚገኝበትን ቦታ ማመላከት አይኖርባቸውም፤

(ረ) ታዳሚዎችን አደንዛዥ እፅ እንዲሞክሩ የሚያበረታታ ለምሳሌም ከእጹ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚመጣን ስሜት በበጎ ጎኑ አሞካሽቶ የሚያቀርብን ማንኛውንም አይነት ሪፖርት ክልከላ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

(ሰ) የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚነትን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዳሉና ከሱስ ባህሪያቶቻቸው ከሚመጡ ጎጂ ውጤቶች ሰዎች ሊጠበቁ እንደሚችሉ መልእክት የሚያስተላልፍ ዘገባን ማጉላት ይኖርባቸዋል፤

(ሸ) ትምባሆና የአልኮል መጠጥ መጠቀም መብት መሆኑን የሚከራከሩ ወገኖች ሲጠቀሱ ስለ ጉዳቱ የሚናገሩ ባለሙያዎች አብሮ ማቅረብ እንደሚገባ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፤

**19/ ምስሎችን እና ስሞችን መጠቀም**

19.1/ እንደአጠቃላይ የመገናኛ ብዙኃን በምስሎችና በስም አጠቃቀሞች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ፤ የሚታተመው ምስል የሚመለከታቸውን ሰዎች ሊጎዳ በሚችልበት ጊዜ ከማተም ወይም ከማሰራጨት መራቅ አለባቸው።

19.2/ የዜናውን እውነታ እና ትክክለኛነት በሚያዛባ መልኩ ምስሎችን ከመጠቀም መቆጠብ አለበት።

19.3/ የሀዘን፣ የአደጋ እና በወሲብ ጥቃት የተጎዱ ሰዎችን ስሜት የሚያሸማቅቁ እና የሚያሳፍሩ ምስሎችን ከማሰራጨት መቆጠብ ይገባል፤

**20/ሰብአዊ ክብርን መጠበቅ**

መገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች የማህበራዊ ደረጃዎችና ባህላዊ ጉዳዮችን የስሱነት ስሜት በመረዳት በዓለም አቀፋዊና በአህጉራዊ ህጎች የተመለከቱትን የሰውን ልጅ መሰረታዊ ነፃነቶችንና መብቶችን ማክበርና መከላከል አለባቸው፡፡ በተለይም መገናኛ ብዙሃን ለሚከተሉት መብቶች ተገቢ የሆነ አትኩሮት መስጠት አለባቸው፡-

20.1/የግል መብት

ሀ. መገናኛ ብዙሃን ጉዳዩ ለእውነተኛ የህዝብ ጥቅም ብቻ ካልሆነ በስተቀር በአንድ ግለሰብ የግል ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባትና ይህን መብት ከሚጥሱ ተግባራት መቆጠብ አለባቸው፡፡

ለ. ከላይ የተመለከተው ቢኖርም አንድ የግል ጉዳይ በህዝብ ዘንድ የታወቀ ጉዳይ ከሆነ በሚዲያው አስተያየት የሚሰጥበት ጉዳይ መሆን ይችላል፡፡

ሐ. ግላዊ መብት የህዝቡን ጥቅም እስካልተቃረነ ድረስ የአንድን ሰው መኖሪያ ቤት፣ ቤተሰብ፣ ሃይማኖት፣ ጤና፣ ፆታዊ ሁኔታ፣ የግል ኑሮና ጉዳዮችን ያካትታል፡፡

መ. የሕዝቡ የማወቅ መብት በሰዎች ግላዊ መብት ላይ የበለጠ ክብደት እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሠ. ጋዜጠኞች ለዚህ ጉዳይ ላይ ዘብ መቆም አለባቸው፡፡

20. 2/ ማስፈራራት

ሀ/ ጋዜጠኞች መረጃ ለማግኘት በማሰብ ሰውን ማስፈራራት፣ ማጎሳቆልና ተቀባይነት የሌለው ያልተቋረጠ ክትትል ማድረግ የለባቸውም፡፡

ለ/ ፈቃደኛ አለመሆኑን እስካሳወቀ ድረስ ጋዜጠኞች አንድን ሰው ጥያቄ መጠየቅ፣ ስልክ መደወል፣ መከታተል ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት የለባቸውም፡፡ ከዚሁ ግለሰብ ይዞታ ላይ እንዳይገኙ ግልፅ ማስጠንቀቂያ እስከተሰጣቸው ጊዜ ድረስ ክትትሉን ማቆም አለባቸው፡፡

ሐ/ አርታኢዎች እነዚህን መርሆዎች በስራቸው የሚሰሩ ሰዎች እንደሚያከብሩ ማረጋገጥ ብሎም ከመርሆዎቹ ውጭ የተገኙ መረጃዎችን ላለመጠቀም መጠንቀቅ አለባቸው፡፡

20. 3/ ጥፋተኛ ተደርጎ ያለመገመት

ሀ/ መገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች አንድ ግለሰብ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት እስካልተረጋገጠ ድረስ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብቱን ማክበር አለባቸው፡፡

ለ/ መገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች አንድ ሰው ከወንጀለኞች ጋር ትውውቅ ያለው በመሆኑ ብቻ እንደ ጥፋተኛ የሚያሳይ አቀራረብ ከመጠቀም መቆጠብ ያለባቸው ከመሆኑም በላይ ንፁህ እስከሆኑ ጊዜ ድረስና እነሱን መጥቀስ ከሚዘገበው ጉዳይ ጋር አግባብነት እስከሌለው ድረስ ጥፋተኛ የተባለውን ግለሰብ ቤተሰቦች ወይም ዘመዶች በስም ከመጥቀስና ምስል ከማሳየት መቆጠብ አለባቸው፡፡

**21/ የዓመፅ ድርጊቶች**

21.1/ መገናኛ ብዙኃን ሁከትን፣ የታጠቁ ዘራፊዎችን፣ ሽፍታዎችን እና የሽብር ተግባራትን ከማቅረብ መቆጠብ አለባቸው።

21.2/ መገናኛ ብዙኃን ማህበረሰባዊ ክፋቶችን፣ የጦርነት ተግባራትን፣ የዘር ወይም የሃይማኖት ግጭቶችን ለማበረታታት ወይም ለማወደስ ለሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም ጽሁፎች ዓምዶቻቸውን ወይም የአየር ሰዓታቸውን ጥቅም ላይ እንዲውሉ መፍቀድ የለባቸውም።

**22/ ማስታወቂያዎች**

22.1/ ዋና አርታኢው የዚህን የሥነ ምግባር ደንብ ተቃራኒ የሆነ ማንኛውንም ማስታወቂያ እንዲሰራጭ መፍቀድ የለበትም።

22.2/ ዋና አርታኢው በዚህ ሕግ መሠረት በሚወጣው የማስታወቂያ የሥነ ምግባር ደንብ መመራት አለበት።

**23/ የጥላቻ ንግግር**

መገናኛ ብዙሃን ጦርነትን የሚያነሳሱ፣ ጥላቻን የሚሰብኩ እና ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርዱ የአደባባይ መግለጫዎችን በተመለከተ በኢፌዴሪ ህገመንግስት የተደነገጉትን ክልከላዎች ያከብራሉ፡፡ በመሆኑም በዘገባዎቻቸው አንድን ሰው በዘር፣ በብሔር፣ በፆታ፣ በሃይማኖት ወይም በፖለቲካዊ አስተሳሰብ ላይ በተመሰረተ ልዩነትና ማናቸውም አይነት አካላዊ ወይም የአእምሮ ህመምን ወይም ችሎታ ማጣትን አስመልክቶ ጥላቻን በሚያበረታታ እንዲሁም ንቀትን ወይም መገለልን ሊፈጥር የሚችል ቋንቋን ከመጠቀም መቆጠብ አለባቸው፡፡

23.1/ ጋዜጠኞች በጎሣ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቀለም እና በጾታ ላይ የተመሠረቱ ሀሳቦችን ሰዎችን የሚያንቋሽሽ ንግግር የሚናገሩ ሰዎችን ማስተናገድ አይገባም።

23.2/ ዘረኛ ወይም ግጭት ቀስቃሽ አሉታዊ የብሔር ተኮር ቃላትን ማስወገድ አለባቸው።

23.3/ ጎሳ ወይም ዘር ላይ ያተኮሩና ዘገባዎች በአጠቃላይ በህዝቡ ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ተፅእኖ እና የአመለካከት ለውጦች በጥንቃቄ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

**24/ ማህበራዊ ሃላፊነት መወጣት**

መረጃዎችን ሲሰበሰቡና ሲያሰራጩ መገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች ለማህበረሰቡ ያለባቸውን ኃላፊነቶች በአጠቃላይ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ጥቅሞች/ፍላጎቶችን ማሰብ አለባችው፡፡

24.1/መገናኛ ብዙሃን የጋራ ሰላምንና ወዳጅነትን ለማሳደግ እጅግ የተለየ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

24. 2/ከሕዝቦች፣ ከብሔረሰቦች ወይም ከሃይማኖቶች ጋር በተያያዘ በሚነሱ አለመግባባቶች/ግጭቶች ላይ የሚሠሩ ዜናዎች፣ አስተያየቶች ወይም ሃሳቦችና እውነታዎች በተገቢው ሁኔታ ከተረጋገጡ በ|ላ መቅረብ ያለባቸው ሲሆን ትኩረታቸው በመፍትሄው ላይ ሆኖ የሕዝቦችን ትስስር፣ ወዳጅነትና ሰላምን ለማስፈን በሚያስችል መልኩ ይሆናል፡፡

24.3/ በአጠቃላይ በተለይም ከሕዝቦች አለመግባባቶች ወይም ግጭቶች አኳያ፡-

ሀ. የሚያነሳሱና ስሜታዊ የሆኑ ርዕሶችን ከመጠቀም መቆጠብ አለባቸው፡፡

ለ. ርዕሶች የታተመውን ወይም በሥራቸው የተዘረዘሩትን ፍሬ ሃሳቦች የሚያንፀባርቁና ምክንያታዊ መሆን አለባቸው፡፡

ሐ. ክሶች /ወቀሳዎችን/ የሚያመለክቱ አረፍተ ነገሮችን የያዙ ርዕሶችን እነዚህ በማን እንደተባሉ ወይም ምንጩን ወይም ክሶቹን /ወቀሳዎቹን/ ቢያንስ በጥቅስ ምልክት ውስጥ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

24.4/ የአሸባሪዎችን ጥቃቶች ወይም የህዝቦች ግጭቶች ወይም የተፈጥሮ አደጋዎችን የሚያሳይ ዜና ሲዘገብ የመገናኛ ብዘሃን አስከሬኖችን የሚያሳዩ አሰቃቂ ምስሎችን ወይም ሌሎች ሽብርን ወይም በህዝቦች መካከል የመነሳሳት ስሜቶችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ፎቶግራፎችን እና ምስሎችን ከማሳተም/ከማስተላለፍ መታቀብ አለባቸው፡፡

24.5/ የሕዝብ ጥቅም በዚህ ደንብ ከተመለከቱት መርሆዎች የበላይነት ያለው ሲሆን በተለይም፡-

ሀ. ወንጀልን ወይም ከባድ ጥፋቶችን መመርመርና ማጋለጥ፤

ለ. የሕዝብን ጤናና ደህንነት የመጠበቅ፤

ሐ. ሕዝቡ በአንድ ድርጊት ወይም በአንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ንግግር በስህተት እንዳይመራ የመከላከል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

24.6/ መገናኛ ብዙኃን የፕሮግራም መርሃ-ግብር መረጃ ለአድማጭ/ተመልካች ቀድመው ማሳወቅ እንዲሁም በተዋወቀው መሰረት ፕሮግራሞችን ማሰራጨት ማክበር፣በተቻለ መጠን የህትመት ቀንን መጠበቅ ይገባል፤

24.7/ መገናኛ ብዙኃን በቀጥታ ስርጭት ለሚተላለፍ ፕሮግራም የተሟላ የቴክኒክ ዝግጅት እና ጥንቃቄ በማድረግ አስቀድሞ ማሳወቅ፤አላስፈላጊ አስተያየቶችና ድምፆች እና ምስሎች አብሮ እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡

24.8/ መገናኛ ብዙኃን በቀጥታ ስርጭት ወቅት ከህግና ከስነ ምግባር ውጪ የሆኑ ክስተቶች፤ንግግሮችና ድምፆች ሊተላለፉ ይችላሉ ብለው ሲገምቱ የማቆያ መሳሪያ (Delay machine) መጠቀም፡፡ ይህንንም ለተደራሲው ማሳወቅ፤ ስህተቶች አገላለፆች ሲያጋጥሙ በፍጥነት ለአድማጩ ወይም ለተመልካቹ ማረሚያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

24.9/ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ዜና ወይም ፕሮግራም ሲያዘጋጁ የታላሚ ታዳሚዎች ፍላጎትና ምኞት ማካተታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ብሮድካስተሩ ለኅብረተሰቡ ጠቀሜታ ያላቸው መልዕክቶች (የተዘጉ የትራፊክ መንገዶች፤ የአደጋ ወይም በሽታ መከላከል መመሪያዎች፣ ተረኛ ፖሊስ ጣቢያና መድሃኒት ቤቶች፣ ሚቲዮሮሎጂ፣ የእሳት አደጋና መከላከልና መሰል አድራሻዎችና የመሳሰሉ መልዕክቶችን ለአድማጭ/ተመልካች ማቅረብን ይመለከታል፡፡

24.10/ በማይድን ህመም ለተያዙና ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች በቂ የአየር ሽፋን መስጠት ይገባል፡፡

## 25/ የሌላውን ሥራ እንደራስ ሥራ ማቅረብ

የሌላ ሰውን ሥራ እንደራስ ሥራ ማቅረብ ከሥነ ምግባር ውጪ መሆኑን የመገንዘብና አንድ አስቀድሞ የተሰራ ሥራ እንደገና በከፊልም ሆነ በሙሉ ሲታተም ወይም ሲሰራጭ የሥራውን ምንጭ የመጥቀስ ግዴታ የጋዜጠኛው ይሆናል፡፡

## 26/ የሕዝባዊ አስተያየት ጥናት

26.1/ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች የሕዝባዊ አስተያየት ጥናት ውጤቶችን ሪፖርት ሲያደርጉ ሕዝቡ የጥናቱን ጥቅምና ዋጋ በአግባቡ ለመፍረድና ለመገምገም እንዲችል አድርገው ማቅረባቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

26.2/ የሕዝባዊ አስተያየት ጥናት ሪፖርቶችን በተቻለ መጠን የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል፡-

(ሀ) የዳሰሳ ጥናቱን በገንዘብ የደገፈ አካል ካለ ማንነቱን መግለፅ፤

(ለ) የተጠየቁትን ጥያቄዎች ቃል በቃል ለይቶ ማመልከት፤

(ሐ) ናሙና የተወሰደበት የኅብረተሰብ ክፍል ትርጉም፤

(መ) የናሙናው መጠንና ናሙናው የተወሰደበት ዘዴ፤

(ሠ) የትኛው ውጤት በከፊል የናሙናው ታሳታፊዎች ለምሳሌም በወንዶች ወይም በሴቶች ወይም የተወሰኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋፊዎች ላይ ብቻ የተመሠረተ እንደሆነ፤ እንዲሁም የመቶኛ ስሌቱ የተመሠረተበትን መነሻ የናሙና ቁጥር መግለፅ፤

(ረ) ናሙናውን ያካሄደው ድርጅት ስም፡፡

26.3/ በተጨማሪም የሚከተሉት መረጃዎች ሊካተቱ ይችላሉ፡-

(ሀ) በአካል፣ በመኖሪያ ቤት፣ በስልክ፣ በኢሜይል፣ ጎዳና ላይ ወይም በሌላ መንገድ መደረጉን ጨምሮ ቃለ-መጠይቆቹ እንዴት እና የት እንደተካሄዱ፤

(ለ) ቃለ-መጠይቆቹ የተካሄዱበት ቀንና ጊዜ፤

(ሐ) የሕዝብ አስተያየቱ በማን እንደሰበሰበ ለምሳሌም በሰለጠኑ ቃለ-ምልልስ አድራጊዎች፣ በስልክ አስተያየት ሰብሳቢዎች፣ በሪፖርተሮች ወዘተ፤

26.4/ ስልክ በመደወል ወይም በኢንተርኔት አማካይነት የሕዝብ አስተያየቱ የተሰበሰበ ከሆነ ውጤቱ የተገኘው በተገቢው መንገድ ስታስቲካዊ ናሙና አወሳሰድ በመከተል እንዳልሆነና ይልቁንም ናሙናው የተዋቀረው በተሰጣቸው ቁጥርና አድራሻ በፈቃዳቸው ምላሽ ከሰጡ ተሳታፊዎች በመሆኑ የጠቅላላ የኅብረተሰቡ ተወካይ ናቸው ብሎ መደምደም እንደማይቻል ግልፅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መንገድ የተጠናቀረ የሕዝብ አስተያየት ጥናት ሪፖርት ሲደረግም የሕዝብ አስተያየት ጥናቱ ውጤቶች የሕዝቡ አስተያየት ማሳያዎች ናቸው የሚል የተሳሳተ አስተያየት የመስጠት እድል ካለው “አብዛኛው ሰው” እና “ሕዝቡ” የሚሉ ገለፃዎችን ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

**27/ የአካባቢ ጉዳዮችን በተመለከተ**

27.1/ መገናኛ ብዙሃን የአካባቢ እንክብካቤን ማበረታታት አለባቸው፡፡

27.2/ መገናኛ ብዙሃን በተለይም ንግድ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚዘገቡ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች በህብረተሰቡ ላይ ስለሚኖራቸው አካባቢያዊ ተፅእኖዎች ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡

27.3/ መገናኛ ብዙሃን የአካባቢ ጥፋቶችን የማጋላጥና የመከላከል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**28/ በዘገባ ጉዳትን መቀነስ**

መገናኛ ብዙሃን የህዝቡን የመረጃ ፍላጎት ከሚያስከትለው ጉዳት ጋር ማመጣጠን ይኖርባቸዋል። ዜናን ተከታትሎ ማቅረብ ተጨማሪ ጉዳት እስካላስከተለ ድረስ መሆኑን መገንዘብ፤ ጋዜጠኝነት ሃላፊነትን ለመሸሸ ወይም አላግባብ ጣልቃ ለመግባት ፈቃድ አይደለም።

**29/ የአርታዒው ኃላፊነቶች**

29.1/ ዋና አርታኢው በህትመቱ ወይም በሚዲያው ላይ የሚወጡና የሚሰራጩ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ ለሁሉም ይዘቶች ኃላፊነቱን ይወስዳል።

29.2/ ኃላፊነቱን መወጣት በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ከሆነ ይኸው ጉዳይ አስቀድሞ በግልጽ መነገር አለበት።

29.3/ በጠቅላላ የመገናኛ ብዙሃን አርታዒዎች ሊከተሏቸው ከሚገቡ የሥነ ምግባር መመሪያዎች ውስጥ፡-

ሀ. በመገናኛ ብዙሃን የሚወጡ መረጃዎች ከአድልዎ፣ ከብልግና፣ ከዘረኝነትና አመጽ ቅስቀሳ የጸዱ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

ለ. በመገናኛ ብዙሃኑ የሚወጡ ጉዳዮች ጥሬ ሃቆች ከአስተያየት መለየታቸውን ማረጋገጥ፤ በማስረጃ የተረጋገጡና እውነተኛ ጉዳዮችን ብቻ ማውጣት፤ አሉባልታዎችን አለማደፋፈር፡፡

ሐ. የስም ማጥፋት ተግባር ያለመኖሩን ማረጋገጥ፡፡

መ. ድርጅቱ ተሳታፊ ሆኖ በተገኘበት የስም ማጥፋት ተግባር ውስጥ ተገቢና ትክክለኛ ምላሽ የተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

ሠ. በዚህ የስነ ምግባር ደንብ ውስጥ የተመለከቱት መርሆዎች በድርጅቱ ውስጥ መተግበራቸውንና መስፋፋታቸውን ማረጋገጥ፤

ረ. የመገናኛ ብዙሃኑ በአገሪቱ ህግና ደንብ መሰረት መሥራቱን ማረጋገጥ፡፡

**30/ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶችና የበላይ ሀላፊዎች ሊከተሏቸው ስለሚገቡ ሥነ ምግባራት**

ሀ. ሠራተኞችን በተለይም አርታኢውን በሙያ ብቃት መሥፈርት ብቻ መቅጠር፡

ለ. በአርታኢው የሙያ ነፃነት ውስጥ ጣልቃ ከመግባት መታቀብ፡፡

ሐ. ሚዲያው የተቋቋመበትን ዓላማ በግልጽ ማስቀመጥ፤

መ. ሚዲያው የሚሰጠውን ግልጋሎትና የሥራ ውጤት አስመልክቶ የህዝብ አስተያየትና ጥያቄዎች ክትትል የሚደረግበትንና መልስ የሚሰጥበትን ሥርዓት መዘርጋት፡፡

ረ. የድርጅቱን ፓሊሲ፣ ዓላማና ታማኝነት ሊጎዳ ከሚችል ስጦታና ምልጃ መጠንቀቅ፡፡

ሰ. በተጨማሪ ስልጠናዎች አማካኝነት ሁሉም ሰራተኞች የሙያ ብቃታቸውን የሚያሻሽሉበትን እድል ማመቻቸት፡፡

ሸ. ሰራተኞች በድርጅቱ ሲቀጠሩ ሊሰጣቸው የሚገባ የድርጅቱ የስነ ምግባር ደንብ እና የስራ ዝርዝር መኖሩን ማረጋገጥ፡፡

ቀ. የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ለድርጊቶቻቸው ለሕዝብ፣ ለሙያውና ለራሳቸው ተጠያቂ እንደሆኑ እውቅና መስጠት፤

በ. ሁሉም ጋዜጠኞችና የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የሙያ ደረጃዎችን አክብረው እንዲሰሩ በንቃት ማበረታታት፤

## ምዕራፍ ሁለት

## የበይነ መረብ ጋዜጠኝነት የሥነ-ምግባር መመሪያዎች

**2/ የበይነ መረብ ጋዜጠኝነትን በተመለከተ**

የበይነ መረብ ጋዜጠኞችና ፈቃድ ያለው ማንኛውም የበይነ መረብ ሚዲያ ተቋም ወይም ጋዜጠኛ ከላይ የቀረቡትን የስነ ምግባር ደንብ ማክበር ያለባቸው ሲሆን በተለየ መልኩ ከዚህ በታች ያሉትን መመሪያዎች ሊከተሉ ይገባል፤

2. 1/ በመርህ ረደጃ  የበይነ መረብ ጋዜጠኝነት የሚተገብሩ ሁሉ የአገልግሎት  መድረኩ ወይም ፎርማት ምንም ይሁን ምን (ድረ ገፅ፤ዩ ቲዩብ፤ ፌስ ቡክ፤ቲውተር፤ኢንታግራም፤ሊንክዲን ወዘተ)ሁሉንም ሙያዊ ስነ-ምግባር እና የጋዜጠኝነት ዋና እሴቶችን ማክበር አለባቸው።

2.2/ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን ተቋማትና ጋዜጠኞች በበይነ መረብ አማካይነት የሚቀርቡ ዜናዎች፤ ፕሮግራሞች፣ ፎቶዎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎች፤ አስተያየቶች፤ ወይም ማስታወቂያዎች የሀገሪቱን ህገ-

መንግስት፣ የመገናኛ ብዙኃን አዋጅን፣ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ፣ የማስታወቂያ አዋጁን፣ የሙያ ስነ-ምግባር መመሪያውን፣ ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ የወጡ ህግጋትን፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎችን እንዲሁም ሌሎች የሀገሪቱን ህጎችን ማክበር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፡፡

2. 3/ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኛ ምንጊዜም ለህግ የበላይነት መቆም ያለበት ሲሆን የሚሰራበት ተቋምም ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ይረዳል፡፡ የሚገኝበትን አድራሻም ሆነ ሌሎች የሚጠቀምባቸውን የማህበራዊ ሚዲያ ስምና የአገልግሎት አይነት በግልጽ ለህዝብ ያስተዋውቃል፤

2. 4/ ማንኛውም የበይነ መረብ ተቋም ወይም ጋዜጠኛ የጥላቻ ንግግርንና የሐሰተኛ መረጃን በአደባባይ ስብሰባዎች በብሮድካስት፣ በህትመት ፣በማህበራዊ ሚዲያዎች፣ በፅሁፍ ወይም በቪዲዮ እንዳይሰራጭ የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡በትብብር ለመስራትና ለመከላከልም ቁርጠኛ መሆን ይኖርበታል፤

2. 5/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ሠጪ በሚያሠራጨው ኘሮግራም ወይም ፅሁፍ ላይ የተደራሲ አስተያየት መድረክ ክፍት ማድረግ ይኖርበታል፤ ሆኖም ከተደራሲ የሚሰጡ አስተያየቶች የሶስተኛ ወገን ስም የሚያጎድፍ ሆኖ ሲገኝ በተቻለ ፍጥነት ከመድረኩ ማስወገድ ይኖርበታል፤

2. 6/ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ሠጪ በሚያሠራጨው ኘሮግራም ወይም ፅሁፍ ስህተት ሲገኝበት ለማረም የሚያስችለውን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል።

2. 7/የበይነ-መረብ የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት ሰጪ ፀያፍና የብልግና ቋንቋ እንዲሁም ፆታን፣ ብሔርንና ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ የጥላቻ ስሜት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርግና ግጭት የሚያነሳሳ ዘገባን ማሰራጨት የለበትም፡፡

2. 8/ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች ከተዛባ መረጃ እና አዛብቶ ከማሰራጨት (Disinformation) ራሳቸው መጠበቅ አለባቸው፤ የተዛባ መረጃ ማለት መረጃው ሙሉ ለሙሉ ውሸት የሆነና አንድን ማህበረሰብ ፣ ቡድን ወይም ግለሰብን በቀጥታ ለመጉዳት ታስቦ ለገንዘብ፣ ለፓለቲካዊ ትርፍ ወይም ሌላ ጉዳይ ውዝግብ ለመፍጠር የሚሰራጭ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ያልተከሰተና ያልተፈፀመ ነገርን እንደተከሰተና እንደሆነ ተደርጎ የሚቀርብበት መንገድ ነው፡፡

2. 9/የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን  የተሳሳተ መረጃ ከማሰራጨት መጠበቅ አለባቸው፤ የመረጃ ማሳሳት ማለት (Misinformation)  ትክክል ያልሆነ መረጃ ሲሆን ነገር ግን ሆን ተብሎ አንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ለማጥቃት የሚፈፀም ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን  መረጃ የሌላን ሰው ሊጎዳ ስለሚችል መረጃውን ፖስት ማድረግ ወይም ለሌሎች ማጋራት አይገባም፡፡

2. 10/የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኛ የተበከለ መረጃን ለሌሎች ከማሰራጨት መቆጠብ አለበት፤ የተበከለ መረጃ  ማለት  (Malinformation) ከፊል እውነተኛ መረጃ  ላይ ውሸት በመጨመር ወይም በትክክለኛ መረጃ ላይ የሐሰት ፎቶ ወይም ቪዲዮ ቀይጦ በማሰራጨት የሚከናወን  ተግባር ነው፡፡

2. 11/ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኛ ራሱ ያላዘጋጀውንና ሃላፊነት ሊወስድበት የማይችላቸውን ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ መረጃን በመቀነስ ወይም በመጨመር ማጋራት አይገባም፤

2. 12/ በበይነ መረብ  በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ከሌሎች መረጃዎች የተለየ መሆኑ በግልፅ እንዲታወቅ ሆኖ መቅረብ አለበት፤ ዜናና ማስታወቂያን ቀላቅሎ ማቅረብ የለበትም፡፡

2. 13/  የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ጥቅሶችን ወይም ተቆርጠው የተወሰዱ ድምፆችንና ምስሎችን ሲጠቀሙ ጉዳዩ መጀመሪያ የቀረበበትን አውድ መጠበቅና የመጀመሪያውን ቃና ሳይለወጥ ለማስተላለፍ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

2. 14/ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ሀሰተኛ፤አሳሳች የተዛቡና የጥላቻ ንግግሮች በሌሎች ቻናሎች ስለመታተሙ ወይም ስለመሰራጨቱ ሲታወቅ የተሰራውን ስህተት ማጋለጥና ትክክለኛውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት በማቅረብ እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፡፡ እርማቱ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የሚሰጡ ማስተባበያዎችን ይጨምራል፡፡

2. 15/ የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች ገንዘብ ለማግኘት በሚል ከይዘቱ ጋር የማይሄዱ ርዕሶችን፤ፎቶዎችንና ተንቀሳቃሽ ፊልሞችን ለመጠቀም መሞከር አይኖርባቸውም፤

2. 16/  በሞባይል ስልክም በሌሎች የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በቀጥታ የሚተላለፉ ይዘቶች  የበይነ መረብ ሚዲያ እና ጋዜጠኞች የሚከተሉትን ህጎች እና መመሪያዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ።

2. 17/ በበይነ መረብ ይዘት እና በተጠቃሚው ለሚመነጨው የአስተያየት መቀበያ በተዘጋጁ መድረኮች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት ሊኖር ይገባል። አርታኢዎች በሶስተኛ ወገኖች በድረ-ገጻቸው ላይ ለሚታተሙ ይዘቶችን መልሰው ለተደራሲያን ሲያቀርቡ ከፍ ያለጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

2.18/ በድረ-ገጽ ይዘት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ hyperlinks ተጠቃሚዎችን ሆን ተብሎ ጎጂ እና ሀሰተኛ መረጃዎችን ወደያዙ ወይም የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ደንብን ወደማያከብሩ ድረ-ገጾች እንዳይመሩ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

2. 19/ የበይነ መረብ አዘጋጆች አስተያየት መቀበያ ሳጥኑን ዘወትር መከታተል እና ህገ-ወጥ የሆኑ መልዕክቶች ፤ የሰውን ክብር የሚነኩ፤ ግላዊነት የሚጥሱ ወይም የጥላቻ ንግግር እንዳይሰራጭበት ወይም እንዳይታተምበት የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

2. 20/ የበይነ መረብ አዘጋጆች ድረ-ገጾቻቸውን ወይም ቻናሎቻቸው በአጭበርባሪዎች እጅ እንዳይገባ የይለፍ ቃሉን ኃላፊነት በሚሰማው ሰው እጅ ብቻ እንዲቀመጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

2. 21/ የበይነ መረብ ባለቤቶች፤ጋዜጠኞችና አቅራቢዎች በሚዲያውና በራሳቸው የግል የማህበራዊ ሚዲያ ገፆች ላይ የሚተላለፉት መልዕክቶች ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ቢገመትም ከህግና ስነ ምግባር ውጪ አለመሆኑን ማጤን አለባቸው፤

2. 22/ በበይነ መረብ አዘጋጆች ወይም ኦፕሬተሮች ጥላቻን ወይም ጥቃትን የሚቀሰቅስ ወይም በፆታ፣ በእድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በቋንቋ፣ በአካል ወይም በአእምሮ እክል፣ በፖለቲካዊ እምነት ፣ በሃይማኖት ፣ ወይም በዘር ወይም ማህበራዊ ደረጃ፤ በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ ቀጥተኛ የሆነ መድልዎ የሚያስከትል ማንኛውንም መረጃ፣ በጽሁፍም ሆነ በእይታ ማተም ወይም ማሰራጨት የለባቸውም።

2. 23/ በማህበራዊ ሚዲያ ሀሰተኛ መረጃ እና የጥላቻ ንግግር የሚያስከትሉትን አሉታዊ ውጤቶች ላይ የህግ ተጠያቂነት እንዳለ ዘወትር ለተደራሲው ግንዛቤ ማስጨበጥ እንደሚገባ መገንዘብ።

2. 24/ የበይነ መረብ አዘጋጆች ተጠቃሚዎች በገጾቻቸው ላይ ቅሬታ ሲቀርብ ምላሽ መስጠትና በገጻቸው ላይ ማተም አለባቸው። ቅሬታ/ማሳወቂያ ሂደቶችን በግልፅ መሳወቅ አለባቸው።

2. 25/ የበይነ መረብ አዘጋጆች የጥላቻ ቃላትና የስድብ ቋንቋ እንዳይነገር የይዘት ማጣሪያዎችን ወይም ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን በተቻለ መጠን መጠቀም ይኖርባቸዋል።

2. 26. የበይነ መረብ አዘጋጆች (የተጎዱት ሰዎች ወይም ሌሎች ወገኖች ቅሬታ ቢቀርብም ባይቀርብም) ተቀባይነት የሌላቸውን ይዘቶች እንዳወቁ ለመመርመር እና ለማስወገድ ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

2. 27/ የበይነ መረብ አርታኢዎች በተደጋጋሚ ግጭት ቀስቃሽ ሀሳቦችንና ጽንፈኛ ቅስቀሳዎችን ወይም አግባብነት የሌለው አስተያየት የሚሰጡ ወይም የሶስተኛ ወገን ሙብትን የሚነኩ አስተያየት ሰጪዎችን በአጠቃላይ ማገድ ይችላሉ።

2. 28. አዘጋጆች እና አርታኢያን በተለይ በግል ክብር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ወሲባዊ ይዘት ያላቸው ወይም የግለሰቦች ስምምነት የሌላቸው ምስሎችን (ፎቶግራፎችን፣ ቪዲዮን ወዘተ) የሚለጥፉ አስተያየት ሰጪዎችን ለመለየት እና በፍጥነት ለማውረድ ልዩ ፖሊሲዎችና ስልቶች ሊኖራቸው ይገባል።

2. 29/ የበይነ መረብ አዘጋጆች ወይም ኦፕሬተሮች በተቻለ ፍጥነት እና ከ 48 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቅሬታዎች ላይ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፤ በተለየ ሁኔታ፣ ይህንን የጊዜ ሰሌዳ በተለይ ከህግ ወይም ከስነምግባር አንፃር በፍጥነት ለመተግበር አስቸጋሪ ከሆነ ለቅሬታ አቅራቢው ተነግሮ ጊዜው ሊራዘም ይችላል።

2.30/ የበይነ መረብ አዘጋጆች የሚዲያቸውን ስም በታዋቂ ሰዎች ስም፤ምስልና ስራ አጅበው አሳሳች ስራ መስራት የለባቸውም፤

2.31/ አዘጋጆች የበይነ መረቡን የአስተያየት ቦታን ለንግድ አካላት ወይም ለትርፍ ዓላማዎች መጠቀምን ወይም የግል ጉዳይን ማስተዋወቂያ መድረክ አድርጎ መጠቀምን የሚከለክሉ ደንቦችን ሊያወጡ ይችላሉ፤

2. 32/ በድርጅቱ በይነ መረብ ድረ-ገጾች ላይ የሚታተሙ የግል ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮዎች ወይም የተፃፉ ጽሑፎችም በሕዝብ ዘንድ የሚዲያው እንደሆኑ ይገመታል፤ ካልሆኑ ወይም የይለፍ ቃሉ በሌሎች እጅ መግባቱ ከታወቀ ወዲያውኑ በሌላ መንገድ ለህዝብ ማሳወቅ ይገባል፡፡

2.33/ ከማህበራዊ ሚዲያ የሚወሰዱ ፎቶግራፎች እና ቪዲዮዎች በጥንቃቄ መመርመር ፤ ተቆርጠው ያልተቀጠሉ መሆናቸውን እና ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

2. 34/ በበይነ መረብ ሚዲያዎች አማካይነት ህፃናት፤ወጣቶችና ሴቶች የሳይበር ጥቃት ሰለባ የመሆን ኢጋጣሚያቸው ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ሁልጊዜ አርታኢዎች ንቁ መሆን አለባቸው።

2. 35/ የበይነ መረብ ሚዲያዎች ቀደም ሲል የታተሙትንና የተሰራጩትን መረጃዎች ይዘታቸውን በተቻለ መጠን ማህደር መያዝ አለባቸው። የህግ ክርክር በሚቀርብበት ወቅት ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲመጣ ሀላፊነቱ የበይነ መረብ ባለቤት ነው፡፡

2.36/ የቅጂ መብትን አለማክበር በሌሎች ሚዲያዎች የተዘጋጁ ይዘቶችን እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ደጋግሞ መጠቀም የቅጂ መብት ጥሰት እና የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን እንደመጣስ ይቆጠራል። በተጨማሪም፣ የሶስተኛ ወገን ይዘት ማንኛውም ጥቅስ (ፍትሃዊ አጠቃቀም) የመረጃው ምንጭ/ደራሲ በግልፅ ማመልከት እና ሌሎች የቅጂ መብት ህግ መስፈርቶችን ማክበር አለበት።

2.37/ የበይነ መረብ አዘጋጆች ሚዲያዎቻቸው ህጋዊ መሆኑን ማረጋገጫ/Verify/ ከሚመለከታቸው ኩባንያዎች ማግኘት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፤

**2.2/ የሥነ ምግባር ደንቡ ተፈጻሚነትና አተረጓጎም**

2.2. 1/ በዚህ ደንብ የተዘረዘሩት የሥነ ምግባር ጽንሰ ሐሳቦች ከኢትዮጵያ ሕገ መንግስት እና የመገናኛ ብዙሃን ዐዋጅ፤ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶችና መርሆዎች እንዲሁም በነዚህ መርሆዎች መሰረት በወጡ እና በተቋቋሙ ዓለምአቀፋዊ ደረጃዎች መሰረት ይተረጎማሉ፡፡

2.2.2/ የዚህ ሥነ ምግባር ደንብ ዓይነተኛ ይዘቶች የበለጠ የጠሩና የነጠሩ፣ የተፍታቱና በየጊዜው የሚከሰቱ ተግባራዊ ግዴታዎችን መመከት የሚችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት አስፈላጊ መሆኑ በታመነ ጊዜ በሰፊ ጥናት ላይ የተመሰረተ ሐሳብና የተሻሻለ ደንብ ይቀርባል፡፡

2.2.3./ ይህ የሥነ ምግባር ደንብ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ወይም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በምክር ቤቱ አባላት ላይ የፀና ይሆናል፡፡

ማጣቀሻዎች


- የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት(1987)
- የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/13
- የኢትዮጵያ ሚዲያ ፖሊሲ /2013
- የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠር የወጣ ዐዋጅ ቁጥር (2013)
- የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት የስነ ምግባር ደንብ (2008)
- የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን የጋዜጠኞች የሙያ የሥነ ምግባርና የአሰራር ደንብ መመሪያ (ያልታተመ)
- በሕፃናት ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ጥቃትና ብዝበዛ የመገናኛ ብዙሃን የስነ ምግባር ደንብ(የኢትዮጵያ፤ኬኒያና፤ታንዛኒያና ኡጋንዳ 2000)
- Best practice Guide for VOA (2019)
- Media Ethics and Self-Regulation in Botswana (2001).
- Code of Conduct for the practice of Journalism in Kenya (2013)
- Self-regulation in India media (2021)
- Media Ethics: A Guide for Professional Conduct, 5th edition(2016)
- Professional code of ethics for journalist and editors by Uganda Media Council (2014)

- Ethical guidelines for online journalism (2018)
- Social media codes of conduct: Reflections for mediators (2020)
- Facebook’s Community Standards,
- Twitter’s Rules and policies,
- YouTube’s Community Guidelines.
- How to be Transparent Online (2021)
- United Nations Support Mission in Libya, Libyan journalists, activists and social media influencers meet in Cairo and agree to combat hate speech, Cairo/Tripoli, 13 November 2019.